## የኢ.ማ.ማ.ተ ዕጩ ተማሪዎች ምዝገባ መስፈርቶች፣ ትዕዛዞችና መመሪያዎች

### ለመርሃ ግብሩ ለማመልከት የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች

- ዜግነት፡ ኢትዮጵያዊ/ዊት
- ፆታ፡ ወንድ/ሴት
- ዕድሜ፡ ትምህርቱ በሚጀምርበት ጊዜ 25 እና ከዛ በታች
- በእንግሊዝኛ ቋንቋ ጥሩ የመናገርና የመፃፍ ችሎታ ያለው/ያላት
- ከፌዴራል ፖሊስ የወንጀል ሪከርድ እንደሌለው/ላት የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል/የምትችል

### የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

- በኤሌክትሪካል ኢንጂነሪንግ፣ በኤሌክትሮ ሜካኒካል ኢንጂነሪንግ፣ ፓወር ኢንጂነሪንግ፣ ኤሌክትሮኒክስና ኮሙኒኬሽን ኢንጂነሪንግ፣ ኤሌክትሪካልና ኮምፒውተር ኢንጂነሪንግ፣ ሜካትሮኒክስ ኢንጂነሪንግ፣ BSc ዲግሪ ያለው/ያላት

### የስልጠና መርሃ ግብሩን ለመቀላቀል የሚያስፈልጉ መግቢያ ደረጃዎችና ቅድመ ሁኔታዎች

### የሚከተሉትን ደረጃዎች በስኬታማነት መጨረስ

### ደረጃ 1፡ የመለየት ሂደት

- በኢ.ማ.ት.ኢ. የሚዘጋጅ የጽሁፍ የመግቢያ ፈተና እንዲሁም ለቃለ መጠየቅ ለመጠራት የተቀመጠውን ዝቅተኛ ውጤት ማስመዝገብ ይጠበቅባቸዋል፤
- የመግቢያ ፈተናውን ካለፉ በኂላ ቃለ መጠይቅ በኢ.ማ.ት.ኢ. የቃለመጠይቅ ጉባኤ ለመርሃ ግብሩ ተቀባይነት ማግኘት ያስፈልጋል

### ደረጃ 2፡ የቅበላና ዋስትና ስምምነት መፈረም

- ዕጩ ተማሪዎችና ዋሶች የቅበላ ስምምነቱን ከመፈረማቸው በፊት የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው፤

### ሰነዶች

- **ከተማሩበት ዩኒቨርሲቲ የዲሲፕሊን ማረጋገጫ ደብዳቤ** - ተማሪው/ዋ በካምፓስ ቆይታው/ዋ ምንም ዓይነት የስነ-ምግባር ችግር እንዳልነበረው/ራት የሚያሳይ
- ስልጠና ከጀመረ/ች ቢያንስ ከስድስት ወር በኂላ የአገልግሎት ጊዜው የሚያበቃ የፀና የቀበሌ መታወቂያ
- ፓስፖርት ካለ
- ከሁለቱም የቤተሰብ ዋሶች ጋር ያለውን የጋብቻ ወይም የስጋ ዝምድና የሚያሳይ ማስረጃ
- ያገባ/ያላገባ ማስረጃ፣ ያገባ/ች ከሆነ የባለቤቱ/ቷ ፊርማና በአካል መቅረብ አስፈላጊ ነው
- ከፌዴራል ፖሊስ የወንጀል ሪከርድ እንደሌለው/ላት የሚያሳይ ማስረጃ

**ፈቃዶች**

- የቅበላ እና የዋስትና ስምምነቶች በሚፈረምበት ወቅት የሚፈፀም "የቅድመ ትንበያ ግምገማ" ለመውሰድ የሚፈቅድ ስምምነት

**ዋሶች**

- ሁለት የቤተሰብ አባሎች
- በእጩ ተማሪው/ዋ እና በቤተሰብ ዋሶች መካከል ያለው ዝምድና ከሶስት ደረጃ የዘለለ መሆን የለበትም፤ ማለትም (እናት፣ አባት፣ እህት፣ የእህት ባል፣ ወንድም፣ የወንድም ሚስት፣ ሴት አያት፣ ወንድ አያት፣ አክስት፣ አጎት፣ የአክስት ልጅ እና የአጎት ልጅ)

**ዋሱ የዋስትና ሰነዱን ከመፈረሙ በፊት የሚከተሉትን ሰነዶች ማቅረብ ይኖርበታል**

- የፀና እና የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ (ዋናው እና ኮፒ)
- ዋሱ/ሷ ያገባ/ች ከሆነ የጋብቻ የምስክር ወረቀት (ዋናው እና ኮፒ)፣ ዋሱ/ሷ ያላገባ/ች ከሆነ የቀበሌ መታወቂያውን ከሰጠው አካል እንዳላገባ/ች የሚገልጽ ማስረጃ ማምጣት አለበት/ባት
- ዕጩ ተማሪው/ዋ እና ዋሶቹ ያገቡ ከሆኑ የእጩ ተማሪው እና ዋሶቹ የትዳር አጋር በአካል ቀርበው የቅበላ/ዋስትና ስምምነቶቹን መፈረም አለባቸው
- ዋሱ/ሷ ከሚሰራበት/ከምትሰራበት መ/ቤት ወርሃዊ ደመወዝ የሚገልጽ (ደመወዝ ከ5,000 ብር ያላነሰ መሆን አለበት)፣ ቋሚ ሠራተኛ መሆኑን/ኗን፣ በተጨማሪም ሠራተኛው/ዋ መ/ቤቱን ቢለቅ/ብትለቅ መ/ቤቱ አስቀድሞ የሚያሳውቅ መሆኑ በደብዳቤው ላይ መጠቀስ አለበት
- የንብረት ባለቤትነት ማረጋገጫ - የቤት ካርታ ወይም የመኪና ሊብሬ
- የፖስታ ሳጥን ቁጥር - ዕጩ ተማሪው/ዋ የሚገኙበት አድራሻ

ለድርጅታችን የሚፃፉ መረጃዎች በሙሉ **"ለኢትዮጵያ ማሪታይም ትሬኒንግ ኢንስቲትዩት"** ተብለው መፃፍ ይኖርባቸዋል።።

**ደረጃ 3፡ የህክምና ምርመራ፡** የህክምና ምርመራው የሚደረገው በአዲስ አበባ እና በባህርዳር ከተማ ብቻ ሲሆን የዋስትና ስምምነቶችን ከመፈረማቸው በፊት ተቋሙ እውቅና በሰጠው ክሊኒክ ብቻ የሚደረግ ይሆናል

**ደረጃ 4፡** የቅበላ እና የዋስትና ስምምነቶች ከተፈረሙ በኂላ በባህርዳር መሠረታዊ የደህንነት ስልጠና የሚደረግ ነው

**ማሳሰቢያ፡** የቅበላ ስምምነቱ የፀና የሚሆነው ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው።

**የኢ.ማ.ት.ኢ. አድራሻ**

- **አዲስ አበባ:**
  - አራዳ ክፍለ ከተማ፣ ቸርችል ጎዳና፣ ትራኮን ህንፃ 8ኛ ፎቅ
  - ስ.ቁ. 0930-00-0621
  - ኢ-ሜይል፡ Bsisay@emacrew.com
- **ባህርዳር፡**
  - ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ፔዳ ካምፓስ፣ ማሪታይም አካዳሚ
  - ስ.ቁ.፥ 0935-98-36-38
  - ኢ-ሜይል፡ ZTeferi@emticorp.com